DC safe
support for empowerment

# ከቤት ውስጥ ጥቃት ለተረፉ ደህንነትና በራስ መተማመን

## የSAFE ተከራካሪ እንዴት ሊረዳዎ እንደሚችል

**ተከራካሪዎች የሚከተሉትን ሊያደርጉልዎት ይችላሉ፣**

- ያሉብዎትን የደህንነት ጭንቀቶች ማወያየት
- በሁሉም የህግ ሂደቶች የመንፈስ ድጋፍ መስጠት
- ስለ ህግ ጥበቃዎች መረጃ መስጠት
- ወደ ሌሎች የህግ፣ ማህበራዊ እና/ወይም የድጋፍ አገልግሎቶች እና የምክር አገልግሎት ሰጪዎች መምራት

**ዓላማችን እራስዎን ከበደል እና ጥቃት እንዲጠብቁ መርዳት እና ድጋፍ መስጠት ነው።**

በማንኛውም ሁኔታ፣

- ማንም ሰው መደብደብ፣ ማስፈራራት ወይም መዋረድ የለበትም
- ጥቃቱን የጀመሩት እርስዎ አይደሉም
- ያለ ፍርሀትና ሁከት የመኖር መብት አለዎት
- ተከራካሪዎች ሊረዱዎት ዝግጁ ናቸው

**Survivors and Advocates for Empowerment (SAFE), Inc.**
PO Box 7412 • Washington, DC 20044 • phone: 202-879-7851 • fax: 202-879-1191 • www.dcsafe.org

# መረጃዎች የቀጠለ...

### የምክር አገልግሎት እና ጉዳይ አፈጻጸም

Wendt Center.................................................. ....204-5021

The Women's Center....................................... .....293-4580

S.O.M.E..................................................................797-8806

### የህግ እገልግሎቶች

Legal Aid Society ............................................... 628-1161

Break the Cycle .................................................. 824-0707

Bread for the City ............................................... 587-0525

AYUDA..................................................................387-4848

Family Law Self Help Center.................................879-1471

DC Crime Victims Compensation........................879-4216

DC Court Clerks Office ........................................879-0157

Child Support -................................................... 879-7868

VINE Victim Information and Notification Everyday 877-329-7894

PG County Sheriff's Office...........................301-883-7005

PG County Family Crisis Center....................301-779-2100

### የሚያነጋግሩት ሰው

Gay & Lesbian National Hotline................1-888-843-4564

National Teen Dating Abuse Helpline...... 1-866-331-9474

National Suicide Prevention Hotline.........1-800-273-8255

ACCESS Helpline:.......................................1-888-793-4357

Crises Outreach Services (DMH mobile clinic) CPEP (አጠቃላይ የሳይካትሪ እና የድንገተኛ ፕሮግራም) 673-9319

National Domestic Violence Hotline ........1-800-799-7233

# የመረጃ ምንጮች

**የቤት ውስጥ ሁከት እና መደበኛ መጠጊያዎች በዲሲ**

ማስታወሻ፣ አብዛኛዎቹ ተጠቂዎች የፖሊስ ሪፖርት ወይም TPO/CPO ካላቸው ለወንጀል ጥቃት ማካካሻ ክፍል ማመልከቻ በማስገባት ጊዜያዊ መጠለያ ያገኛሉ።

ከዚህ በታች ለተጠቀሱት ጊዜያዊ መጠለያዎች አብዛኛውን ጊዜ እነኚህን ሰነዶች ማሳየት አያስፈልግዎትም፣

House of Ruth ....................................................667-7001
Ext 515 (women with children) ext 240 (single)
Shelter Hotline .........................................(800) 535-7252
Calvary Women's Shelter...................................289-2111
Mary House .......................................................635-9025
Sasha Bruce (youth only) ...................................675-9340
DASH...................................................................462-3274
Virginia Williams (homeless families)..................202-724-3932
Homelessness Shelter Hotline...................800-535-7252
St. Ann's Maternity Home (teen mothers).......301-559-5500

## የቤት ውስጥ ጥቃት ለደረሰባቸው ከዲሲ ውጭ ያሉ መጠለያዎች

ያስታውሱ፣ እነኚህ መጠለያዎች እንደ ዲሲ መጠለያዎች የሌላ አካባቢተጠቂዎችን ሁልጊዜ ላይቀበሉ ይችላሉ።

Doorways (in VA).....................703-237-0881
Bethany House (in VA)............703-658-9500
ACTS-Turning Points (in VA)................703-221-4951
Family Crisis Center (PG County MD) .........1-866-382-7474
House of Ruth—MD (Baltimore MD).................410-889-7884
SARC (Bel Air MD)...................................410-836-8430

## ቀጥሎ ምን ማድረግ?

ሁኔታውን ለፖሊስ ሪፖርት ማድረግ ቢወስኑም ወይም ባይወስኑም ከሰኞ እስከ ዓርብ በመደበኛ የሥራ ሰዓቶች (8:30 am-4:30 pm) ወደ አንዱ የቤት ውስጥ ጥቃት መመዝገቢያ ማዕከል (DVICs) መሄድ ይችላሉ። እንግዳ መቀበያው ቦት ለሚቀመጡት ሠራተኞች ከOCAP ተከራካሪ ጋር መነጋገርዎን ይንገሩ።

## የቤት ውስጥ ጥቃት መመዝገቢያ ማዕከል(DVIC)

የDVIC ተከራካሪዎች የሚከተሉትን ያደርጋሉ፤:

- ስለ ጊዜያዊ እና/ወይም ሲቪል ጥበቃ ትዕዛዝ መረጃ ይሰጡዎታል እንዲሁም እንዲያገኙ ይረዱዎታል
- ስለ ህግ፣ የወንጀል እና የሲቪል ፍርድ ቤትን ጨምሮ፣ ስለ ህግ ሂደት መረጃ ይሰጡዎታል
- ከሚያስፈልግዎት እርዳታ ጋር ያገናኙዎታል። ይህም ለራስዎ እና ለልጆችዎ፣ ምክር፣ ቤት፣ ጊዜያዊ መጠለያ፣ እንደ የወንጀል ሰለባ ካሳ የመሳሰሉ ድርጅቶችን ያካትታል
- በአጠቃላይ ሂደቱ ደህና መጠለያ እና ቤት እንዲያገኙ ይረዱዎታል
- ስለ እራስዎ ወይም ልጆችዎ ያሉ የደህንነት ችግሮችን ይከታተሉልዎታል

**DC Superior Court**
**500 Indiana Avenue, NW Suite 4550**
**Washington, DC 20001**
**Phone 202-879-7857**
**Fax 202-879-1191**
Judiciary Square Metro—Red Line
Archives/Navy Memorial—Yellow and Green Line

**United Methodist Hospital**
**1310 Southern Avenue, SE**
**Medical Services Building, Room 311**
**Washington, DC 20002**
**Phone 202-561-3000**
Southern Avenue Metro—Green Line

# የቤት ውስጥ ጥቃት ምንድነው?

የቤት ውስጥ ጥቃት በሌላው ሰው ላይ ሥልጣን እና ቁጥጥር ለማግኘት የሚደረግ የባህርይ ምሳሌ ነው። ለረጅም ጊዜ የሚደረግ ጥቃት ባህርይ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ጥቃት ጊዜ ባለፈ ቁጥር ተደጋጋሚና የከፋ ይሆናል።

የቤት ውስጥ ጥቃቶች በተለያዩ ሁኔታዎች ይከሰታሉ። የአካል ጥቃት፣ እንደ በጥፊ መምታት ወይም መግፋት፣ ስሜታዊና የሳይኮሎጂ ጥቃት፣ እንደ ስድብ፣ መጮህ ወይም ከቤተሰቦችዎ እና ጓደኞችዎ ማለያየት ሊሆን ይችላል። ንብረትዎን ማጥፋትን እና ለደህንነትዎ ወይም በአካባቢዎ ላሉ ልጆችዎ ወይም እርስዎን የሚረዱ ሰዎችን ጨምሮ የሚያሰጋ ዛቻን ሊያካትት ይችላል።

ምንም ሆነ ምን፣ አንድ ነገር በአዕምሮዎ ሊኖር የሚገባው፣ ጥቃት የእርስዎ ጥፋት አይደለም -- ማንም ሰው መጠቃት የለበትም። በቤተሰብ ውስጥ ጥቃት በጭራሽ ተቀባይነት የሌለውና ህገ-ወጥ ተግባር ነው።

## ማስታወሻዎች

## ሰነድ ማስቀመጥ

ጥቃት ፈጣሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ተጠቂዎቹ ምናልባት ሪፖርት ካደረጉ ወይም ሲያደርጉ ታማኝነት ለማሳጣት ዋሽተው ተጠቂውን ያሳጣሉ። የጥቃቱን ዓይነት በተቻለ መጠን በሰነድ በመያዝ እና አጥቂው አግኝቶ እንዳይጥለው በማህደር ውስጥ ደህና ቦታ በማስቀመጥ እራስዎን ይጠብቁ፡

በሰነድ አያያዝ መንገዶች፣

- የጥቃት ድርጊቶቹን በማስታወሻ ወይም በቀን መቁጠሪያ ይያዙ፣ ያለፉ ጥቃቶችን የቻሉትን ያህል ወደ ኋላ ተመልሰው እስከሚያስታውሱበት ጊዜ ለመጻፍ ይሞክሩ። በተጨማሪም ጥቃቱ ሲፈጸም ያዩ ወይም የሰሙ ምስክሮችን ስም እና አድራሻዎችን ይመዝግቡ።
- አጥቂው ለእርስዎ የደወለበትን ስልክ ቁጥር ጨምሮ የስልክ ጥሪዎችን እና የቴክስት መልዕክቶችን በማስታወሻዎ ወይም በቀን መቁጠሪያዎ ላይ ይጻፉ። የስልክ ኩባንያዎን የጥሪ ዝርዝሮችዎን እንዲሰጥዎት ይጠይቁ።
- የጉዳትዎችዎን ሁኔት የሚያሳዩ ሁኔታዎችን፣ የቴክስት መልዕክቶችን፣ የተሰበሩ ንብረቶችን፣ ወዘተ... ፎቶግራፍ ያንሱ። አስፈላጊ ከሆነ የDVICs ተከራካሪዎች ፎተግራፍ አንስተው ሊያስቅምጡልዎት ይችላሉ።
- እርስዎ ዝርዝሩን በማስታወሻ መጻፍ ካልቻሉ ወይም አስጊ ከሆነ፣ ሌላ የሚያምኑት ሰው መዝገቡን እንዲያስቀምጥልዎት ይጠይቁ፣ እና አዳዲስ እንቅስቃሴዎች ከተፈጠሩ ያስታውቁት።
- ሁሉንም የፍርድ ቤት ሬኮርዶች፣ የሲቪል እና የወንጀል ጉዳዮችን ጨምሮ፣ የህክምና ሪኮርዶችን፣ ከዶክተርዎ፣ ቴራፒስት ወይም በድንገተኛ የታከሙበትን መረጃ እና ከተከራካሪ ድርጅቶች የተጻፉልዎትን የድጋፍ ደብዳቤዎች በአንድነት ደህና ቦታ ያስቀምጡ።
- አዲስ ጥቃትን ለፖሊስ ያስታውቁ እና ለእያንዳንዱ አዲስ ጥቃቶች አዲስ የፖሊስ ረፖርት ቁጥሮች ያግኙ እና/ወይም ለ CPO ረፖርት አድርገው ከሆነ የየጊዜውን መረጃ ከማመልከቻው ጋር ያያይዙ።
- ከአጥቂዎ የተላኩ የኢሜል፣ ፌስቡክ ወይም ሌላ የኦንላይን ግንኙነቶችን አትመው ደህና ቦታ ያስቀምጡ።
- ከአጥቂዎ የሚደርሱዎትን ዛቻዎች፣ የድምጽ መልዕክቶች፣ ወይም የቴክስት መልዕክቶች አይሰርዟቸው!

ምንም እንኳን ይህንን ማድረግ ብዙ ሥራ መስሎ ቢታይም፣ ለወደፊት ጊዜ ሊያድንልዎት እና እርዳታ በሚያስፈልግዎ ጊዜ ጥቃቱን ለማሳየት/ለማረጋገጥ ይረዳዎታል።

## የጥቃት ፈጻሚ ባህሪዎች

የተለየ ተደባዳቢ የለም። ተደባዳቢዎች ከሁሉም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መነሻዎች፣ ዘሮችና ኃይማኖቶች ይመጣሉ። የሚያጠቁ ሰዎች የሚከተሉትን ያደርጉ ይሆናል፣

መቆጣጠርን የማጣት ፍራቻ

በኃይማኖታዊ የፆታ ኃላፊነቶች ያምናሉ

ዝቅተኛ የሆነ በራስ መተማመን

የመንፈስ ጭንቀት የሚመጣው ከውጭ በተከሰቱ ሁኔታዎች ነው ብለው ያምናሉ

ከማህበራዊ ሁኔታ የገለሉ የሆኑ ይሆናሉ

ወላጆቻቸው እርስ በርስ ሲጣሉ አይተዋል ወይም በልጅነታቸው ጥቃት ደርሶባቸው ይሆናል

እውነተኛ ያልሆነ የግንኙነት ግምት አላቸውታቸው

ለራሳቸው ችግር ወይም ቅጥጥር ለሌላቸው ሁኔታዎች ሌላውን ይኮንናሉ

የሚታዩ ምልክቶች:

ከመጠን ያለፈ ቅናት እና እራስ ወዳድነት

ተቆጣጣሪ ጠባይ

በፍጥነት መወዳጀት

ከዕውነት የራቀ ግምት

ማግለል

በእንስሳት ላይ መጨከን

***ለሌላ ሰው ጠባይ ኃላፊ አይደሉም፣ ስለሆነም ጥቃት ሊደርስብዎ አይገባም።***

## የጥቃት ስልቶች

**ማስገደድ እና ማስፈራራት፣** እርስዎን የሚጎዱ ነገሮች ማድረግ፤ እሄዳለሁ ወይም እራሴን እገድላለሁ ብሎ ማስፈራራት፤ እራስን ህገ ወጥ ወይም አሳፋሪ ነገሮች እንደተፈጸመ ማድረግ።

**ማስፈራራት፣** የተለያዩ ገጽታዎችን፣ ድርጊቶችን፣ እና/ወይም ምልክቶች በመጠቀም ማስፈራራት፤ ንብረት መደምሰስ፣ መሣሪያዎች ማሳየት።

**ስሜታዊ ጥቃት፣** እራስህን ዝቅ ዝቅ ማድረግ፣ ስለራስህ መጥፎ ስሜት እንዲኖርህ ማድረግ፣ እራስህን እብድ እንደሆንክ ማሰብ፣ እራስህን ማዋረድ፣ እራስህን መኮነን።

**ገለልተኝነት፣** የምታደርገውን፣ የምታነጋግረውን ወይም የምታየውን መቆጠብ፤ የምትሄድበትን መገደብ፣ የምታደርገውን ተገቢ ለማስመሰል ቅናትን መጠቀም።

**ማቃለለ፣ መካድ፣ መዝለፍ፣** ጥቃቱን ማቃለል፣ ለችግርህ ትኩረት አለመስጠት፣ ጥቃቱ አልተፈጸመም ማለት፣ የጥቃቱ መነሻ እኔ ነኝ ማለት።

**በልጆች መጠቀም፣** ስለ ልጆችህ እራስህን ጥፋተኛ ማድረግ፣ ልጆችን መልዕክት እንዲያደርሱ መጠቀም፣ ጉብኝትን በመጠቀም እራስን ማዋከብ፣ ልጆችን እወስዳለሁ ብሎ ማስፈራራት።

**የኢኮኖሚያዊ ጥቃት፣** ሥራ ከማግኘት/ከመቆየት መከላከል፣ አበል እንዲሰጡህ በሥራ ቦታ ማስፈራራት፣ ገንዘብ መውሰድ፣ ገንዘብ እንድትጠይቅ ወይም ገንዘብህን እንድትሰጥ ማድረግ።

**ልዩ መብት፣** እራስህን እንደ የቤት አገልጋይ መቁጠር፣ ሁሉንም ትላልቅ ውሳኔዎች ማድረግ፣ በግንኙነት እና በቤት ውስጥ ኃላፊነቶችን መወሰን።

## የግል የደህንነት ጥቆማዎች

**ጠብ ሲከሰት**

- ከወጥቤት፣ መታጠቢያ ቤት፣ ወይም አደገኛ፣ ስለታማ ነገሮች ካለበት ማንኛውም አካባቢ መራቅ።
- በቀላል ለማምለጥ የሚችሉበትን መንገድ ያቅዱ። በፍጥነት እና ጉዳት ሳይደርስ መውጣት የሚቻልበትን በር ወይም መስኮት ይምረጡ።
- እርስዎን እና ልጆችዎን ሊረዳ የሚችል ጎረቤት፣ ጓደኛ ወይም ቤተሰብ ይፈልጉ።
- ምን እየተደረገ እንደሆን ልጆችዎን እና ሌሎችን የሚያስጠነቀቅ የመግባቢያ ቃልና በቅድሚያ የታቀድ ፕላን ያዘጋጁ።

**የኑሮ ጓደኛዎን ትተው መሄድ ካሰቡ ለደህንነትዎ ዕቅድ ያውጡ**

- እያንዳንዱ ሁኔታ የተለያየ ነው! ስለ ደህንነት ዕቅድዎ ከተከራካሪዎ ጋር ይነጋገሩ። በደንብ ካልታቀደ ጥሎ መሄድ ለእርስዎና ለልጆችዎ አደገኛ ሊሆን ይችላል። .
- ጥቂት ገንዘብ ያስቀምጡ። በየሳምንቱ የሚያጠራቅሙት ገንዘብ ትንሽ ቢሆንም፣ የራስዎ የሆነ ገንዘብ እንዲኖርዎት ያስፈልጋል።
- ቁልፎችዎን፣ የኪራይ ውሎችን እና አስፈላጊ ወረቀቶችን አባዝተው ከሚያምኑት ሰው ቤት ይስቀምጡ።

**እራስዎ በደህንነት የሚቆዩባቸው መንገዶች**

- የበርዎችዎን ቁልፎች ይለውጡ እና/ወይም የጥበቃ መሣርያ ያስገቡ
- ስለ ህግ መብቶችዎ ተከራክሪዎን ይጠይቁ። ጠቃሚ ህጋዊ ሰነዶች ካሉዎት ምንጊዜም ከእርስዎ አይለዩዋቸው።
- ስለ TPO/CPOs ጎረቤቶችዎን፣ ጓደኞችዎን፣ የሥራ ጓደኞችዎን፣ አከራይዎን እና ቤተሰብዎን እንዲያውቁ ያድርጉ፣ ኮፒ አድርገውም ይስጧቸው።
- ስለደህንነት እቅድ ልጆችዎን ያስተምሩ እና ከልጆችዎ ጋር ልምምድ ያድርጉ።
- አካባቢዎ ላሉ ሰዎች የቀድሞ ጓደኛዎን ፎቶግራፍ ያሳዩ። ወደ አካባቢው ከመጣ/ች 911 እንዲደውሉ ይንገሯቸው።

**ገንዘብዎን እና ማንነትዎን መጠበቂያ መንገዶች**

- የሚስጥር ቃል ኢሜልዎን፣ ባንክ፣ ስልክ፣ ቁስቁሶችዎን እና ሌሎች አካውንቶችዎን ይጠብቃል። የሚስጥር ቃልዎን በየጊዜው ይለውጡ
- በስምዎ ሌላ አካውንት አለመከፈቱን በክሬዲት ሪፖርትዎ ያረጋግጡ
- አጠራጣሪ ሁኔታዎችን ለኩባንያውና ለፖሊስ ያስታውቁ
- የግል ወይም ማንነትዎን የሚገልጹ መረጃዎች ወይም ፎቶ እንደ Myspace ያሉ የማህበራዊ ድህረ ገጾች ላይ አያውጡ። ልጆችዎም እነኝህን መረጃዎች እንዳያወጡ ያረጋግጡ። ይህ በተለይ ጠቃሚ የሚሆነው አካባቢው የሚለቁ ከሆነ፣ አጥቂው መረጃዎቹን ተጠቅሞ ሊያገኝዎ ሊሞክር ስለሚችል ነው።

## የቤተሰብ ፍርድ ቤት እራስ አገዝ ማዕከል JM 570

የቤተሰብ ፍርድ ቤት እራስ አገዝ ማዕከል በፍቺ፣ የልጅ ጥበቃ፣ ጉብኝት እና የልጅ ድጋፍ ጉዳዮች ጠበቃ ለሌላቸው አጠቃላይ የህግ መረጃ ያለቀጠሮ የሚሰጥበት ማዕከል ነው። ማዕከሉ የህግ ምክር አይሰጥም እንዲሁም በፍርድ ቤት ለማንም በጥብቅና አይቆምም።

ማዕከሉ የሚከተሉትን ያደርጋል፣

- ስለ ዲሲ የቤተሰብ ህግ ጉዳዮች መረጃ ይሰጣል
- ስለ ህጋዊ መብቶችዎ እና ግዳጆችዎ ያስረዳዎታል
- የህግ አማራጭዎችዎን ይገልጹልዎታል
- የትኛዎቹ ቅጾች ለእርስዎ የበለጠ ተገቢ እንደሆኑና እንዴት እንደሚሞሏቸው ያስረዱዎታል
- ስለ ፍርድ ቤት ሂደት እና ምን እንደሚጠብቁ ይገልጹልዎታል
- ወድ ሌሎች ክሊኒኮች እና ፕሮግራሞች ይመሩዎታል

**Family Court Self-Help Center**
**Superior Court Building, room JM-570.**
**ሰኞ እስከ ዓርብ፣ 8:30 am to 5:00 pm**
*ማንም ሰው ከ 4:30 በኋላ አገልግሎት አያገኝም

## የወንጀል ሰለባዎች ካሳ ፕሮግራም

የወንጀል ሰለባዎች ካስ ፕሮግራም (CVCP) ኃይለኛ ጥቃት ለደረሰባቸው እና ቤተሰቦቻቸው ዕርዳታ ይሰጣል። CVCP በወንጀል ምክንያት አገልግሎት ላገኙ ክፍያ ይሰጣል።

VCP የሚከፍልላቸው አንዳንድ ወንጀል ነክ ወጪዎች የሚከተሉት ናቸው፣:

- ሀክምና እና መድሃኒቶች
- የአእምሮ ጤና ምክር
- የደሞዝ እጦት
- ጊዜያዊ ድንገተኛ መጠለያዎች (እስከ 30 ቀኖች ድረስ)
- የመጓጓዣ ወጭዎች (እስከ $1,500)
- መስኮቶችን፣ በሮችን እና ለደህነነት ሲባል የቁልፍ መለወጫዎች

ስለ CVC ከጠበቃዎ ጋር መነጋገር ይችላሉ፣ ወደ ሌላ መምሪያ መጠየቅ እና የካሳ ማመልከቻ መጠየቅ ይችላሉ። ብቁ ለመሆን አንዳንድ መረጃዎች የመከራከሪያ ፖሊስ ሪፖርት ግልባጭ ወይም TPO/ CPO ያስፈልግዎታል።.

**Crime Victims Compensation Program**
**DC Court Building A**
**515 5th Street NW, Room 109**
**Washington DC 20001**
**202-879-4216 (Monday—Friday 9am-5pm)**

## የዝምድና ጥያቄ (ፈተና)

| አዎ | የለም | |
|---|---|---|
| | | እርስዎ ወይም ልጅችዎ ጓደኛዎን ትፈራላችሁ? |
| | | ጓደኛዎ ቤተሰቦችዎን እና ጓደኞችዎን ከማየት ያግዳችኋል? |
| | | ጓደኛዎ አቀራረብዎንና ድርጊትዎን ያንቋሽሻል? |
| | | ጓደኛዎ የግል ንብረትዎን አጥፍሮብዎት ያውቃል? |
| | | ጓደኛዎ ያለፈቃድ የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲያደርጉ አስገድድዎት ያውቃል? |
| | | ጓደኛዎ በየጊዜው ይመረምርዎታል እና እንቅስቃሴዎችዎን ይወስናል? |
| | | ጓደኛዎ ጓደኞችዎ፣ ቤተሰቦችዎ ወይም የማያውቋቸው ሰዎች ፊት ያሳፍርዎታል? |
| | | ጓደኛዎ ያስፈራራዎታል፣ በኃይል ይይዝዎታል፣ ይወረውርዎታል፣ ያንቅዎታል ወይም የመታዎታል? |
| | | ጓደኛዎ ገንዘብ እንዲኖርዎት ወይም ሠርተው ገንዘብ እንዳያገኙ ያደረዎታል? |
| | | ስለ ጓደኛዎ አጥቂነት አንዳንድ ጊዜ ላለመናገር አንዳንድ ጊዜ ይዋሻሉ? |
| | | ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት ወይም በመዳራት ይከሰዎታል? |
| | | ጓደኛዎ የዕጽ መውሰድዎን ወይም ኤች አይቪ ሁኔታዎን በመጠቀም ቁጥጥሩ ስር ለማድረግ ይጠቀምበታል? |
| | | ጓደኛዎ ያላችሁን ግንኙነት ለማፍረስ ይቃወምዎታል ወይም ለብቻዬ መሆን እፈልጋልርሁ ሲሉት ይቀበልዎታል? |

**የጥበቃ ትዕዛዝ መረጃ**

**የሕዝብ የጥበቃ  ትዕ ዛዝ (CPO) ምንድነው?**

CPO የረጅም ጊዜ ሀጋዊ ጥበቃ የሚሰጥዎት በዳኛው የሚፈረም ወረቀት ነው።  CPO እስከ አንድ ዓመት ጽኑ ይሆናል፤ ወደ ፍርድ ቤት በመሄድ ሊራዘም ይችላል።  CPOs የእርስዎን ፍላጎቶችን ለማሟላት ሊደረግ ይችላል፣ ማለትም እርሶዎን እና የሚያፈቅሯቸውን ከአጥቂው ነፃ የሚያደርጋቸውን የጥበቃ ዓይነት መጠየቅ ይችላሉ።

***እርስዎ = ከሳሽ*** ***ተከሳሽ = መልስ ሰጪ***

CPO የሚከተሉትን ማድረግ ይችላል፣

- አጥቂው እንዳይደባደብ እንዳያስፈራራ፣ እንዳያጠቃ ወይም እንዳያዋከብ ትዕዛዝ ይሰጣል
- ተከሳሹ ከእርስዎ፣ ከቤትዎ፣ ከሥራዎ ቦታ እና ከማንኛውም እርስዎ አዘውትረው ከሚገኙበት ቦታ (እንደ የዶክተር ቢሮ ወይም የጓደኛዎ ቤት) እንዳይደርስ ትዕዛዝ ይሰጣል
- ተከሳሹ በማንኛውም ዓይነት መንገድ እንዳይገናኝዎ፣ ሦስተኛ ወገንንም ጨምሮ፣ ወይም ግንኙነቱን በተወሰነ መንገድ እንዲያደግር (ለምሳሌ በቴክስት መልዕክት ብቻ  እንዲያድረግ ትዕዛዝ ይሰጣል
- ለአካለ መጠን ላልደረሱ ልጆች ጊዜያዊ የልጅ አደራ ይሰጣል
- ባለአደራ ላልሆኑት ወላጅ የጉብኝት ፈቃድ ይሰጣል
- የልጅ ድጋፍ ይሰጣል
- በአንዳንድ ሁኔታዎች ተከሳሹ ቤቱን እንዲለቅ ትዕዛዝ ይሰጣል
- ተከሳሹ የቤት ውስጥ ጥቃት ግልግል፣ የአደንዛዥ ዕጽ ህክምና ወይም ሌሎች ዓይነት ግልግሎችን ያዛል

**ጊዜያዊ የጥበቃ ትዕዛዝ (TPO) ምንድ ነው?**

- TPO ለ14 ቀናት ብቻ የሚቆይ ከCPO ጋር ተመሳሳይ የሆነ ትዕዛዝ ነው። አብዛኛውን ጊዜ አደጋ በተፈጠረ ጊዜ ለCPO የፍርድ ቤት ቀጠሮ እስከሚሄዱ ድረስ ጥበቃ የሚሰጥዎት ነው። TPO የCPO ማመልከቻ በገባበት ቀን ተጠይቆ በዛው ቀን የሚሰጥ ትዕዛዝ ነው። አስፈላጊ ከሆነ TPO መታደስ ይችላል።  በCPO የሚሰጡ እፎይታዎች ሁሉ በTPO በኩልም ይገኛሉ።

**CPO እንዴት ነው የሚያገኙት?**

1. አቤቱታ (ጥያቄ) በአንዱ የቤት ውስጥ ጥቃት መመዝገቢያ ማዕከሎች ማስገባት
2. ለተከሳሽ ወረቀቶች እንዲላኩ በማድረግ
3. ከሁለት ሳምንት በኋላ ፍርድ ቤት ዳኛው ፊት መቅረብ

***እርስዎ = ከሳሽ*** ***የክስ ወረቀት ያስገቡበት ሰው = ተከሳሽ***

**የፖሊስ ሪፖርት ወይም እስራት ባይኖርም  CPO ማስገባት ይችላሉ።**

**የጥበቃ ትዕዛዝ ምንም ክፍያ የለውም።**

| **ጊዜ** | **ሲቪል** | **የወንጀል** |
|---|---|---|
| **3-6 ወራቶች በኋላ** | ከእርሰዎ ምንም አይጠበቅም | • የወንጀል ፍርድ<br>• ጥፋቱ ከተፈጸመ ከ3-6 ወራቶች በኋላ የወንጀል ፍርዱ ላይ ምስክርነት መስጠት ኖርብዎታል።  ስለ መጭው የፍርድ ቤት ቀጠሮ የአሜሪካ አቃቤ ህግ የተጠቂዎች ተከራካሪ ቢሮ እንዲደውሉ እንመክራለን። |
| **ከፍርድ በኋላ በማንኛውም ጊዜ (አጥቂው ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ)** | ምንም | • ከፍርዱ በፊት የተጠቂ ማስረጃ ያስገቡ<br>• የፍርድ መስሚያ ቀን ይኖርል |
| | • ፖሊስ ይጥሩ<br>• ወደ ምዝገባ ማዕከል ይሂዱ<br>• የማስከበሪያ ማመልከቻ ማስገባት | • ጥቃቱን የፈጸመው አምልጦ ካልሆነ የጥሰቱን ሰነድ/የአጥቂውን መያዝ ለፖሊስ ደውለው ይወቁ።<br>• ወደ ምዝገባ ማዕከል ይሂዱ<br>• ለተጠቂ ተከራካሪዎ  እና/ወይም ለህግ አስከባሪው ደውለው ምን እንደተደረገ ይንገሩ<br>• አጥቂውን ለመያዝ በፍርድ ቤት እንዲመሰክሩ ይጠየቁ ይሆናል |
| **ከሁለተኛው ጥቃት ሁለት ሳምንት በኋላ** | • Go to Contempt Hearing | ምንም |

## የዜጋ ክስ ከወንጀል ክስ ሲነፃፀር

- የዜጋ ክስ **በእርስዎ** የሚደረግ ነው
- በቤት ውስጥ ጥቃት የወንጀል ክስ በእርስዎ የሚደረግ **አይደለም፤** በመንግሥት የሚደረግ ነው

| ጊዜ | የዜጋ | የወንጀል |
|---|---|---|
| **ቀን 1: በቤተሰብ መሀከል ጥቃት ሲፈጠር** | ፖሊስ ይጥሩ። ፖሊስ ባይጠሩም የጥበቃ ትዕዛዝ ያገኛሉ። | ፖሊስ መጥራት አለብዎት። ፖሊስ በአጥቂው ላይ ክሶች ማቅረብ አለበት። ወዲያውኑ ፖሊስ አለመጥራት መረጃ ሊጠፋ ስለሚችል የመታሠሩን ዕድል ሊቀንሰው ይችላል። |
| **ቀን 2: በሚቀጥለው የሥራ ቀን ወይም የተቻለውን ያህል ወዲያውኑ** | ● ወደ አንዱ የቤት ውስጥ ጥቃት ማዕከሎች ይሂዱ። ● CPO ያስገቡ ● ዳኛው በዛው ቀን TPO እንዲያስተላልፉ ይጠይቁ ● ስለ ልጅ አደራ እና የልጅ ድጋፍ ከአንድ ሰው ጋር ይነጋገሩ። | ● አጥቂው ታስሮ ከሆነ ጠዋት ከUSAO የስልክ ጥሪ ይጠብቁ። ● ከተከራካሪ ጋር ለመነጋገር እና ከMPD/USAO ጋር ለመገናኘት ወደ አንዱ የቤት ውስጥ ጥቃት ምዝገባ ማዕከል ይሂዱ። |
| **ከሁለት ሳምንታት በኋላ** | ● የዜጋ ጥበቃ ትዕዛዝ የቀጠሮ ቀን ● በአቤቱታው ላይ በተጠቀሰው ቀን (አብዛኛውን ጊዜ ከሁለት ሳምንት በኋላ) ከዳኛው ፊት ለመቅረብ ወደ ፍርድ ቤት መሄድ አለብዎት፡፡ ዳኛው አንዴ ትዕዛዙን ካስተላለፈ በኋላ አጥቂው ትዕዛዙን ካልጣሰ በስተቀ ወደ ፍርድ ቤት መመለስ የለብዎትም። | ● የወንጀል ጉዳይ የቀጠሮ ቀን ● የማግባባት ጥያቄ የፍርዱን ማቃለል አማራጭ ጨምሮ ● የፍርድ ቀን የጊዜ ሰሌዳ ይያዙ ● የጉዳይ ቀን ቀጠሮ አብዛኛውን ጊዜ ክሱ ከቀረበበት በሁለት ሳምንት አካባቢ ይደረጋል - እርስዎ መገኘት የለብዎትም |

## አገልግሎት

የሲቪል ጉዳይዎ እንዲቀጥል፣ የሚከሱት ሰው (“ተከሳሹ”) ክስ እንዳለበት የሚገልጽ ህጋዊ ማስታወሻ ማግኘት እና ፍርድ ቤት ለCPO ቀጠሮ መገኘት አለበት። ይህ “መጥሪያ” ይባላል። የፍርድ ቤት ወረቀቶች ለተከሳሹ መላክ አለበት። ተከራካሪ በአንዱ የቤት ውስጥ ሁከት ማዕከል ስተገናኙ አገልግሎቱን እና ያሉትን አማራጮች ይገልጽልዎታል።

## CPOዎች እና TPOዎች መጥሪያው ለተከሳሹ እስከአልተላከ ድረስ ማስከበር አይቻልም!

**ለተከሳሹ መጥሪያ መስጠት የሚችለው ማን ነው?**

- ምስክር ያልሆነ ሰው፣ አቤቱታውን ካቀረቡት ውስጥ ያልሆነ እና ዕድሜው ከ18* በላይ መሆን አለበት
- የእፖሊስ ኦፊሰር
- የግል መጥሪያ ሰጪ

*የጥሪ ምላሹ ቅጽ መጥሪያውን ለተከሳሹ የሰጠው ሰው መፈረም እና ለCPO ቀጠሮ ቀን መቅረብ አለበት

**መጥሪያ መቀበል ያለበት ማን ነው?**

- ክስ ያቀረቡበት ሰው
- ማንኛውም ዕድሜው 18 ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ከተከሳሹ ጋር የሚኖር
- የተከሳሹ ቀጣሪ

**የማይፈቀደው ምንድነው?**

- ማስታወቂያውን በፖስታ ቤት በኩል መላክ
- ተከሳሹ ሊያየ ይችላል ብለው የሚያስቡብት ቦታ መለጠፍ
- ከተከሳሹ ጋር አብሮ ለማይኖር ጓደኛ፣ የሥራ ባልደረብ ወይም የቤተሰብ ዓባል መስጠት

**ተከሳሽ የሚከተሉትን ባያደርግም መጥሪያው ጽኑ ይሆናል፣**

1. ማስታወቂያውን ባይወስደው
2. ማስታወቂያውን ባያነበው
3. ማስታወቂያውን ባይፈርመው

**ተከሳሽ የሚከተሉትን ባያደርግም መጥሪያው ጽኑ ይሆናል፣**

1. ቢጥለውም
2. ማስታወቂያውን ቢቀደውም

በCPO ቀጠሮ ቀን የተሞላውን እና የተፈረመውን የመጥሪያ ምላሽ እስካመጡ ድረስ

## ሂደቶቹ ካልተሟሉ የጥበቃ ትዕዛዝ ማግኘት አይችሉ ይሆናል!

## የጥበቃ ትዕዛዝ መጣስ

የእርስዎ TPO ወይም CPO ከተላለፈ በኋላ መጣስ ወንጀል ነው! ለእያንዳንዱ ትዕዛዙን መጣስ አጥቂዎ እስከ 6 ወሮች መታሰር ወይም $1,000 ይቀጣል።

**የCPOን ግልባጭ በየሄዱበት ቦታ መያዝ አለብዎት። የትዕዛዙን ግላባጮች ለጎደኞችዎ፣ ቤተሰብ፣ የሥራ ባልደረባዎች፣ አከራይ፣ የደህንነት ሠራተኞች እና ለልጆችዎ ትምህርት ቤት መስጥት ጥሩ ሀሳብ ነው።**

- ተከሳሽ CPOን ቢጥስ፣ እሱ/ሷ የፍርድ ቤቱን ትእዛዝ ባለማክበር ነው።
- ተከሳሽ CPOን ከጣሰ ልክ እንደ ማንኛውም ወንጀል ፖሊስ ሊያስረው ይችላል።
- ተከሳሽ ካስፈራራዎት፣ አደጋ ላይ ከጣለዎት፣ ካስፈራራዎት ወይም ከጎዳዎት ወዲያውኑ 911 ይደውሉ!
- ወደ DVIC መሄድና CPO እንዲከር ለዳኛው ማመልከቻ ማስገባት
- የአለማበር የቀጠሮ ቀን ወደ ፍርድ ቤት ይሂዱ ወይም ስለጥሰቱ ሪፖርት ከፖሊስ ጋር ይከታተሉ።

> ያስታውሱ፣ TPO ወይም CPO ጥቃቱን አያቆመውም፣ ሆኖም መወሰድ ያለበት ጠቃሚ ሂደት ነው። ለደህንነትዎ እቅድ ለማውጣት ሌሎች ሂደቶችን እንደሚወስዱ ማሰብዎን ያረጋግጡ!

## አጥቂው ካልተለያዘ

## የፖሊስ ሪፖርቶች አመዳደቦች!

ፖሊሶች አጥቂዎን የማሰር እርምጃ ለመውስድ የቤተሰብ መረበሽ ሪፖርት ሳይሆን የጥቃት ሪፖርት (እንደ መደበኛ ድብደባ፣ ንብረት ማጥፋት፣ ወዘተ..) መውሰድ አለባቸው። የቤተሰብ ረብሻ ሪፖርት የቤት ውስጥ ሁከት መፈጠሩን የሚያስይ የጽሁፍ ማስረጃ አይደለም።

## ማስጠንቀቂያዎች

**ፖሊሱ ጥቃቱ የደረሰበት ቦታ ሲመጣ አጥቂው ሄዶ ከሆነ፣**

- ፖሊሱ የፖሊስ ሪፖርት አስገብቶ ለመከታተያ የሪፖቱን ቁጥር ይሰጥዎታል።
- ሪፖርቱ ወንጀሉ የከሰተበት ፖሊስ ጣቢያ ለሚገኝ የቤት ውስጥ ሁከት መርማሪ (ዲቴክቲቭ) ይሰደዳል
- መርማሪው ወንጀሉን ተመልክቶ ለአጥቂው የእስራት ማስጠንቀቂያ መስጠት ወይም አለመስጠት ይገባ እንደሆነ ይወስናል
- ጉዳይዎ ለመርማሪ ከመሰጠቱ በፊት አጥቂዎን ካዩ እና/ወይም መርማሪው ማስጠንቀቂያ ከመላኩ በፊት ከሆነ፣ "ሁለተኛ በቦታው እንዲያዝ" ለመጠየቅ 911 መደወል ይችላሉ

**በሪፖርት ላይ ክትትል ለማድረግ፣**

- ከ2-3 ቀናቶች ውስጥ ሪፖርትዎ ሪፖርቱ ለተወሰደበት ግዛት የቤት ውስጥ ሁከት መርማሪ ይሰጣል
- ሪፖርቱ የተላከበት ግዛት በመደወል ሪፖርቱ ለማን እንደተሰጠ እና የተሰጠውን መርማሪ ማነጋገር ይችሉ እንደሆን መጠየቅ ይችላሉ። ያስታውሱ፣ መርማሪው አንዳንድ ጊዜ የተለያዩ መደበኛ ያልሆኑ ሰዓቶች፣ እንደ እኩለ ሌሊት፣ ሊሠራ ስለሚችል በመደበኛ የሥራ ሰዓቶች ሊያገኙት አይችሉ ይሆናል
- ስለ ጉዳዩ ጥያቄዎች ለመመለስ መራማሪው የመያዝ ማስጠንቀቂያ ለመስጠት እንዲያስችለው በሚፈልግዎት ጊዜ ሁሉ መገኘት ጠቃሚ ነው።
- አዳዲስ የቤት ውስጥ ጥቃት ወንጀሎች (የስልክ ጥሪ፣ ዛቻ) ከተከሰቱ ወይም የበለጠ መረጃ ከተገኘ፣ ለመርምሪዎችዎ አዲስ የሪፖራት ቁጥሮች እና መረጃ ለመስጠት ይደውሉላቸው።

## ሁለተኛ ጊዜ በቦታው መገኘት

ተከሳሹ ተመልሶ እቤትዎ ቢመጣ፣ ፖሊስ ይጥሩ። እሱ/ሷ "ለሁለተኛ ጊዜ በቦታው በመገኘቱ/ቷ" ይታሰራል/ትታሰራለች። ፖሊስ ተመልሶ ሲመጣ፣ ከዚህ ቀደም የተወሰደውን የፖሊስ ሪፖርት የCCN# ቁጥር (የፖሊስ ሪፖርት ቁጥር) ያስፈልጋል።

## የፖሊስ ሪፖርቶች አመዳደቦች!

ፖሊሶች አጥቂዎን የማሰር እርምጃ ለመውሰድ የቤተሰብ መረበሽ ሪፖርት **ሳይሆን** የጥቃት ሪፖርት (እንደ መደበኛ ድብደባ፣ ንብረት ማጥፋት፣ ወዘተ..) መውሰድ አለባቸው። የቤተሰብ ጥቃት ሪፖርት የቤት ውስጥ ጥቃት ሁከት መፈጠሩን የሚያሳይ የጽሁፍ ማስረጃ አይደለም።

## አጥቂው ተይዞ ከሆነ

አጥቂው ተይዞ ከሆነ፣ እሱ/ሷ ወደ አቅራቢያው ፖሊስ ጣቢያ ይወሰዳል/ትወሰዳለች። በቤት ውስጥ ሁከት ምክንያት የታሠሩ ሰዎች ከመለቀቃቸው በፊት ዳኛ ፊት መቅረብ አለባቸው። አብዛኛውን ጊዜ አጥቂው ማታውኑ እስር ቤት አድሮ/ራ በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ፍርድ ቤት ይቀርባሉ። በሰንበት ቀናቶች፣ አጥቂው ቅዳሜ ጠዋት ዳኛው ፊት ይቀርባል ወይም እስከ ሰኞ ጠዋት መቆየት ይኖርበታል።

**መያዝ አጥቂዎን ለአጭር ጊዜ ከቤትዎ ያስወጣልዎታል ወይም እሱ/ሷን አጠገብዎ ከመድረስ ይከላከልልዎታል።**

የአሜሪካ አቃቤ ህግ ቢሮ (USAO) ጉዳዩን ፍርድ ቤት ለማቅረብ ወይም ላለማቅርብ ይወስናል። አብዛኛውን ጊዜ ይህ ውሳኔ የሚወስደው የእርስዎን ፍላጎት ሳይጨምር ነው። ህግ ፊት ለማቅረብ **ካልፈለጉ** ፣ ተከሳሹ ያለምንም ግዴታዎች ይለቀቃል እና እሱን/ሷን በተመለከተ ምንም ዓይነት ክስ ወይም የወደፊት የፍርድ ቤት ቀጠሮ ቀኖች አይኖሩም።

እነሱ አጥቂዎን ህግ ፊት ለማቅረብ ከፈለጉ፣ አጥቂዎ በታዘዘበት/ችበት ቀን ፍርድ ቤት ለመቅረብ ቃል ከገባ/ች ከፍርድ ቀን በፊት ከእስር ቤት ይለቀ/ትለቀቅ ይሆናል። አጥቂዎ አስቀድሞ ክስ ከሌለበት፣ በቁጥጥር ስር ካልሆነ/ች ወይም ጊዜያዊ መለቀቅ (በወረቀት) ላይ ካልሆነ፣ ወይም በቤት ውስጥ ሁከት ምክንያት የተያዘ/ዘች ካልሆነ በስተቀር፣ እስር ቤት አይገቡ ይሆናል። አጥቂዎ ፍርድ እየጠበቀ ባለበት ጊዜ ውስጥ ከተፈታ/ች፣ ፍርድ ቤቱ የወንጀል ጥበቃ ትዕዛዝ ወይም የወንጀል ከእርስዎ እንዲሪቅ/ርቅ ሊያዝ ይችላል።.

አጥቂዎ ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ/ች፣ የደብደባ ህክምና እንዲካፈል/ትካፈል፣ ፕሮቤሽን ላይ ወይም እስር ቤት ይገባ/ትገባ ይሆናል።

ተከራካሪዎ የወንጀል ጉዳይ መረጃዎን ግልባጭ፣ የወንጀለኛ ያለመድረስ ትዕዝዝን ጨምሮ እንዲያገኙ ሊረዳዎት ይችላል።

**ያስታውሱ፣ የወንጀለኛ ማገጃ ትዕዛዝ፣ ከዜጋ ጥበቃ ትዕዛዝ ጋር አንድ አይደለም።**

## የሜትሮፖሊታን ፖሊስ መምሪያ (MPD)

ፖሊስ በህግ የሚከተሉትን እንዲያደርግ ይጠበቅበታል፣

- ከማንኛውም የቤት ውስጥ ጥቃት አቤቱታ በኋላ ወይም የቤት ውስጥ ጥቃት ተደርጓል ከተባለ ሪፖርት ማዘጋጀት
- ቦታውን ከመልቀቁ በፊት የሪፖርት ቁጥር (CCN) መስጠት
- በማንኛውም በምታነጋግሯቸው ጊዜ ስምና የመታወቂያ ቁጥር መስጠት

የኮሎምብያ ዲስትሪክት የግዴታ እስራት ህግ አለው፣ ይህም ማለት፣ ፖሊስ በማሰር ወይም አጥቂው ቦታውን ለቆ ሄዶ ከሆነ እንዲያዝ ማስጠንቀቂያ በማስገባት የተጠቂውን ደህንነት የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት። ለማሠር በቂ መክንያት መኖሩን ፖሊሱ መመርመር አለበት።

*ለማሠር በቂ ምክንያት ከተገኘ፣ የሁለቱንም ወገን ፍላጎት ምንም ቢሆን፣ ኦፊሰሮቹ እንዲያስሩ ህጉ ይጠይቃል።*

**MPD ኦፊሰሮች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ማንንም ስለዜግነት መጠየቅ የለባቸውም።**

## የስደተኛ ጉዳዮች

ለስደተኛ ሴቶች እና ሴት ልጆች ቀጥተኛ የህግ አገልግሎቶች እና ማህበራዊ አግልግሎቶች ወደ ሌላ መምሪያዎች የህግ እና የማህበራዊ አገልግሎት ድርጅቶች፣

| | |
|---|---|
| AYUDA | 202-387-4848 |
| Tahirih Justice Center | 703-575-0070 |
| DVRP (Asian/Pacific Islander) | 202-464-4477 |